# ቴዲ  አፍሮ

*የኮራ ባገር የተዋበ፣*
*ሀቅ ያወቀ ቀልብ የሳበ።*
*ያገር ኩራት የአንድነት ፈርጥ፣*
*የእናቴ ልጅ የሕዝቤ ጌጥ።*

*በመረዋ ድምጽህ ፍቅር በሚሰብከው፣*
*ባለ ቅኔው ብዕርህ እውቀት የሚያፈልቀው።*
*በዜማ ቅኝትህ ነብስ በሚዘራ፣*
*የፍቅር ሳምባዲና ደምቀህ የምትበራ።*
*አልሞላለት ላለው ቀን ከሴት ለለፉ፣*
*ኑሮ ለታከተው የምትሆነው ተሥፋ።*
*ኩራዝ ሻማ ፋና ቀንዲል፣*
*የጥበብ ሰው  ምጡቅ ጸዳል።*
*ንዋይ ንቀህ ሕዝብ አክብረህ፣*
*«አበባ አየሁ» ስትል «ለምለም» ባልንህ፤*
*የቂም ጦር ሰብቀው ሊያሳንሱህ፣*
*የቅጥፈት ምላሳቸውን ቢያሾሉ፤*
*አንተ ሥርየትን ለማኝ ለሁሉ።*

*ያገር ኩራት የአንድነት ፈርጥ፣*
*የእናቴ ልጅ የሕዝቤ ጌጥ።*
*የሰላም ምልክት ዘንባባ፣*
*የፍቅር አርማ ነህ አበባ።*
*የሆዴን አውቀህ የልቤ እንዲደርስ፣*
*እንባ ጉንጨን እስኪያርስ።*
*ልብህን ነክቶ የስደት ጦስ፣*
*ያዜምክልኝ «ምን ይገዥ ልመለስ»።*
*ይቅር እንድትለኝ እማማ፣*
*ሀዘኔን የከፈልህ በዜማ።*

*ባልና ሚስት ሁለት ከፍሎ፣*
*ቢለያያቸው የቀን ጎዶሎ፤*
*ቃልን ማን ሊነጥለው ችሎ።*
*ፍቅርዋን ከውሻ ላሳነሱባት፣*
*የተሰፋ ቃልን የሰጠሀት።*
*ብሶቴን የውስጤን የጮሀክልኝ፣*
*ብለህ ላልከዳሽ ቃል አለብኝ።*
*እኔም ላልከዳህ የቃል ውል ገባሁ፣*
*ምን ኩራት ሊኖረኝ መከታዬን ካጣሁ።*

*ቴዲ ወንድሜ አለኝታዬ፣*
*ያገር ጌጤ መኩሪያዬ።*
*አገር ሙሉ ነህ እልልታ፣*
*ሕዝብ አጃቢህ ሕዝብህ መከታ።*
*በቂም ቋያም ብትቃጠል፣*
*የነርሱ መንገድ ያንተ አይደል።*

*ቢጎበኛቸው የምህረት ዐይን፣*
*ለነርሱም ስርየትን ለምን።*

*የኮራ ባገር የተዋበ፣*
*ሀቅ ያወቀ ቀልብ የሳበ።*
*ያገር ኩራት የአንድነት ፈርጥ፣*
*የእናቴ ልጅ የሕዝቤ ጌጥ።*
*አንተ ባገር ሙሉ ነህ በመንደሩ፣*
*ራሳቸውን በአጋዚ ጦር ያሰሩ፣*
*ያፈሩ እነርሱ ናቸው ዐይን የፈሩ፤*
*ቴዲ ፍቅር ነህ የልጅ ጠቢብ፣*
*በሼመንደፈርህ የምትሰብ።*
*የእስላም የክርስትያኑን ህብር፣*
*እውነቱን ይፋ እምትናገር።*

*በጥፋት ጅራፍ እየተነዱ፣*
*የክህደት ቁልቁለትን የሚወርዱ።*
*እርባና ቢስ ሸንካላ የሀሳብ ቆማጣ፣*
*ጠቋቁመው የመጡ የዘር የጎጥ ቁምጣ፤*
*የትውልድ ዝቃጮች ናቸው የረከሱ፣*
*የሰው ቅማሎች አገር የሚያኮስሱ።*

*እንዳይሆን ብትፈራ ጅብ ከሄደ ውሻ፣*
*ኡኡታ ስታሰማ ቢሆነን ብለህ መነሻ።*
*አሳብህ ከአንተ ገዝፎ ቢፈሩ፣*
*ግዑዝ አካልህን ቃሊቲ አሰሩ።*
*አልሰማ ብዬ አረግሁህ እንጂ ባለተራ፣*
*ኡ ኡ ብለህ ነበር ወጥተህ ከተራራ።*
*አዎ እኔን ብትቀየምም በጥፋቴ፣*
*ቢወቅጡት እምቦጭ ውህነቴ።*
*እለት በእለት አገር ያሉትን እየለቀሙ፣*
*አንድ ባንድ ሲያፍኑ ሲኮረኩሙ።*
*«አገር ትቼ መኖር እፈራለሁ፣*
*ታድያ እስከመቼ እችላለሁ»።*
*ብለህ በሆንክልን  የፍቅር መብራት፣*
*ጨመሩህ አንተን ጭለማ ቤት።*
*በስምህ ስም ተጋርቶ፣*
*ልቡ ከሌላ ሸፍቶ።*
*ሰው ሆኖ ሰው ያልወደደው፣*
*እርሱ እንጂ ነው የታሰረው።*

*ቴዲ ኩራት ነህ የአንድነት ፈርጥ፣*
*የኢትዮጵያ ልጅ የሕዝብህ ጌጥ።*
*የሰላም ምልክታችን ዘንባባ፣*
*የፍቅር አርማችን ነህ አበባ።*

ፍቅር፣ አንድነት፣ ነፃነትና ሰላምን መዘመር ወንጀል በሆነባት ሀገር በመፈጠሩ ፍዳውን ለሚቆጥረው ወጣት ኢትዮጵያዊ ወገናችን ለቴዲ አፍሮ የተጻፈ።

ከትንሣዔ
ነሐሴ 2000